# የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

## ጋዜጣዊ መግለጫ

## በሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ላይ የሚካሔደው ማሸማቀቅ፣ ወከባ እና እሥራት ይቁም!!

ነሐሴ 26 ቀን 2008 ዓ.ም.

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም መሆኑ ይታወቃል። ሰመጉ ከተቋቋመበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 24 ዓመታት ሁለንተናዊ ሐገራዊ የሰብዓዊ መብቶች ተልዕኮ በመያዝ፣ በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ በነደፋቸው በርካታ የሰብዓዊ መብቶች መርሐ ግብሮች አማካኝነት የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትን እና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲጎለብትና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲዳብር የበኩሉን አስተዋጽዖ አበርክቷል፣ እያበረከተም ይገኛል።

ይህን ተልዕኮውን ለማሳካት ሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ፣ የጥሰቱ ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁ፣ የሰብዓዊ መብት ግንዛቤ በሕዝብና በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት ዘንድ እንዲዳብር፣ የተፈጸሙ ጥፋቶች ትምህርት ተወስዶባቸው እርማት እንዲያገኙ ሁኔታና አቅም በፈቀደለት መጠን ብዙ ሠርቷል፣ እየሠራም ይገኛል።

ሰመጉ ሥራዎቹን የሚያከናውነው ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በጽናት በቆሙ ሠራተኞቹ እና አባላቱ ብርቱ ጥረት ሲሆን፣ ከዚህ በታች ስማቸው በዝርዝር የቀረበው ግለሰቦች በሰመጉ አባልነታቸው በየአካባቢያቸው የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እንዲከታተሉ፣ እንዲያጣሩና ሪፖርት እንዲያደርጉ ከሰመጉ ዋናው ጽ/ቤት በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት ሥራቸውን በማከናወን ላይ እያሉ ከሐምሌ ወር 2008ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ቀናት ለእሥር ተዳርገዋል።

1. አቶ ተስፋ ቡራዩ፡- (ዕድሜ 65) በሰመጉ የምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር፡፡ ነሐሴ 8 ቀን 2008ዓ.ም ቀን ታሥረው ከቤተሰቦቻቸውና ከሕግ አማካሪያቸው ጋር እንዳይገናኙ ተደርገው ቆይተው ነሐሴ 11 ቀን 2008ዓ.ም ተፈትተዋል፡፡

2. አቶ አበበ ዋኬኔ፡- በሰመጉ የምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ አባል፡፡ ከነሐሴ 6 ቀን 2008ዓ.ም አንሥቶ ክስ ሳይመሠረትባቸው በኦሮሚያ ክልል ዲጋ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ታሥረው ቆይተው ነሐሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም በአምስት ሺህ ብር ዋስ ተፈትተዋል፡፡

3. አቶ ተስፋዬ ታከለ፡- በሰመጉ የሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና በሰሜን ወሎ ዞን ወልዲያ ከተማ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ አባል፡፡ ነሐሴ 08 ቀን 2008ዓ.ም ታሥረው ባለባቸው የዲስክ መንሸራተት ሕመም ምክንያት በማግሥቱ ቤተሰቦቻቸው የሕክምና ማስረጃ አቅርበው ወደ ሕክምና ተወስደዋል፡፡

4. አቶ ቡልቲ ተሰማ፡- (ዕድሜ ከ50 በላይ) በሰመጉ የምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና ነጆ ከተማ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ቆርጠው የሚታገሉ የሰመጉ ንቁ አባል፡፡ ከሐምሌ ወር 2008.ዓም አንሥቶ በቂሊንጦ ማረሚያ ቤት በእሥር ላይ ይገኛሉ፡፡

ሰመጉ፤ ሕይወታቸው ለአደጋ የተጋለጠ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾችን፣ የአመራሮቹን፣ የአባላትና ሠራተኞቹን ኹኔታ እየተከታተለ ይፋ የሚያደርግ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ያስታውቃል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በመከታተል ሕጋዊ ተግባር ላይ እያሉ ተይዘው በእሥር ላይ የሚገኙት ከላይ የተጠቀሱት የድርጅቱ አባል ባስቸኳይ ከእሥር እንዲለቀቁ፣ እንዲሁም በአባሎቻችንና በሠራተኞቻችን ላይ በተለያየ መንገድና ሁኔታ የሚደረገው ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ እና ወከባ እንዲቆም ሰመጉ በአፅንዖት ይጠይቃል፡፡ ይልቁንም መንግሥትም ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ጥበቃ የማድረግና ድጋፍ የመስጠት ዓለም አቀፍ ግዴታውን እንዲወጣ ሰመጉ አበክሮ ይጠይቃል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)
ነሐሴ 26 ቀን 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ
አዲስ አበባ